ይድረስ፡- በቅዱሱ ኪዳን ወንድሜና የክህነት ባልደረባዬ ለኾንኸው፡
ለኪዳናዊ ዮናስ አበበ።

በፌስ-ቡክ የጎዋ መድረካችን ላይ ላቀረብሃቸው፡ ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎችህ፡ አጫጭር ማብራሪያዎች የኾኑትን መልሶች፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ በቅደም ተከተላቸው ተራ አሥፍሬና በነባር ሰነድ ቅጽነት ዐትቤ ልኬልሃለሁ።
በቅዱሱ ኪዳን ወንድምህና የክህነት ባልደረባህ፡-
ኪዳናዊ ኤርምያስ [ዘአኵስም-ጽዮን]።

**በፌስ-ቡክ ላይ፡ ከኪዳናዊ ዮናስ አበበ የቀረቡ ጥያቄዎች፡-**

ከዚህ በታች ላሠፈርኳቸው፡ ላልገቡኝ ነገሮች፡ የተቻለህን ያህል መልስ እንደምትሰጠኝ፡ አስቀድሜ በማወቅ፡ "እግዜር ይስጥልኝ!" እያልኩ ነው።

፩. የአባታችን ኢየሱስ መሲህ የልደት ቀን መስከረም ፩ ነው፡፡ እንዲሁም የተጠመቀው በ፴ ዓመት። እንዲህ ከኾነ የ፴ኛ ዓመቱ ልደት፡ መስከረም ስለሚኾን፡ የጥምቀት በዓሉ ለምን መስከረም ፩ አልኾነም?

፪. በለውጥ ዕድገት ይትበሃል (Theory of Evolution) እንደሚታመነው፡ ጥንታዊ ሰብአዊ ፍጡር (Hominoidea) ተብለው የሚጠሩ፡ አእባነ አዕፅምት እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ታድያ! እነዚህን አስመልክቶ አንዳንድ ወገኖች፡ "በጥፋት ውኃ የነፈሩ አጥንቶች ናቸው!" ይላሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ያላት አቋም ምን ይመስላል?

፫. ስለ ኢትዮጵያውያን ትክክለኛ የተዋሕዶ አኗኗር የሚተርከው፡ የቶማስ ሞር መጽሐፍ፡ በኪዳናዊት መስከረም ለቺሳ፡ በኢትየጵያኛ ተተርጉሞ፡ ለገበያ መቅረቡ ይታወቃል፤ በመጽሐፉ ውስጥ ስላለው ቀንዳም (ባለ ቀንድ) አንበሳ፡ የምታውቀው ነገር ካለህ፡ ብታሳውቀኝ?

፬. "ዛጔዎች" ተብለው የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አጼዎችን፡ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት፡ ከ"ኢትዮጵያውያን ነን!" ከሚሉ መነኮሳት ጋር በመተባበር፡ መለኮታዊውን የዘውድ ዙፋን፡ ወደሰውኛው ለውጠው፡ "የሰሎሞን ዘር ነን!" ለሚሉት፡ ወደሹመት አቅርበዋል፡፡ ከእነዚህም ዋነኛው ግንባር ቀደም ተዋናይ፡ አቡነ ተክለ- ሃይማኖት ነበሩ፤ ታድያ! ይህን ምግባራቸውን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንዴት ታየዋለች?

**ከኪዳናዊ ዮናስ አበበ ለቀረቡ፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች፡ የተሰጡ መልሶች፡-**

፩. አንተ እንዳልኸው፡ እንደመጽሓፉ ቃል፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ የተጠመቀው፡ በ፴ ዓመቱ ስለኾነ፡ የጥምቀት በዓሉ፡ መስከረም ፩ ቀን ከሚውለው፡ ከልደት በዓሉ ጋር መከበር እንዳለበት የታወቀና የታመነበት ነው።

በመስከረም ፮ ቀን የኾነው ልደቱ፡ እርሱ በተወለደባት፡ በቤተ-ልሔምና ይህችው ቤተ-ልሔም በምትገኝበት፡ በዚያ ክፍለ-ዓለም፡ በረዶው እጅግ በሚጸናበት፡ በታኅሣሡ ወር ማለቂያ ጊዜ ሊኾን እንዳልቻለ ኹሉ፡ ጥምቀቱም፡ የሦስት ቀኖች ልዩነት ብቻ ባለው፡ በዚያው፡ በረዶው እጅግ በሚጸናበት፡ በጥሩ ወር መግቢያ ጊዜ (በጥር ፮፥ ወይም፡ ባዕዳኑ እንደቀየሩት፡ በጥር ፲፮ ቀንም) ሊኾን እንደማይችል የታወቀ ነው።

ጥምቀቱ፡ ከመስከረም ፮ ቀን፣ ተቀይሮ፡ በጥር ፮ ቀን እንዲከበር ያደረጉት፡ የቀደሙት የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው። ይኸውም፡ ኹለቱ ታላላቅ መለኮታውያት [የልደቱ እና የጥምቀቱ] በዓላት፡ በአንዱ፡ በመስከረም ፮ ቀን፡ ዐብረው ከሚከበሩ ይልቅ፡ ሥነ-ፍጥረት የመከር በረከቷን አብዝታና አትረፍርፋ በምትሰጥበት፥ ሕያዋን ፍጥረታትም፡ በመለኮታዊው ሓሤት በሚጥለቀለቁበት፣ የበጋው ወራት መግቢያ በኾነው፡ በጥር ወር እንዲኾን በመወሰናቸው ነው።

ለዚህ ውሳኔያቸው፡ ዋና መግቢያና ተጨማሪ ምክንያት ያደረጉት፤ "**ሰንበትሰ፡ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት፤ ወአኮ ሰብእ፡ በእንተ ሰንበት። ወወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ፡ እግዚአ ለሰንበት።** ሰንበት፡ ስለሰው ተፈጥሮአል እንጂ፡ ሰው፡ ስለሰንበት አልተፈጠረም። የማርያም ልጅም፡ የሰንበት ጌታዋ ነው!" ደግሞም፡ "**ይከውንኬ በሰንበት፡ ገቢረ ሠናይ።** ስለዚህ፡ በሰንበት፡ መልካም መሥራት ይገባል!" ባለበት፡ በዚሁ፡ መመሪያው ውስጥ፡ "**ምጽዋተ አበድር፡ እመሥዋዕት!** ለእኔ፡ መሥዋዕትን ከምታቀርቡልኝ ይልቅ፡ ለተቸገረው፡ ምጽዋትን ብትሰጡልኝ [ማለትም፡ ምሕረትን ብታደርጉለት] እወድዳለሁ!" ብሎ የጠቀሰው የነቢያት ቃሉ፡ የ"**በዓል አከባበራችን**" ሥርዓት፡ በትክክለኛው መልኩ፡ የሚፈጸምበት ምግባር፡ እንዲህ መኾን እንደሚገባው የማመልከቱን ነገር ብቻ አይደለም። (ማቴ. ፲፪፥ ፮-፲፪። ማር. ፪፥ ፳፯-፳፰።)

ነገር ግን፡ ከዚህ በተጨማሪ፡ በምሥራቹ የአዲስ ኪዳን መጽሓፍ ውስጥ፤ በተለይም፡ የሉቃስ በኾነው ክታብ፣ በምዕራፍ ፫፥ ቁጥር ፲፳ ላይ፡ "**ወየአክል ሠላሳ ክረምቱ፡ ለእግዚእ ኢየሱስ፤** ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በዚያ በጥምቀቱ ጊዜ፡ ዕድሜው፡ ሠላሳ ዓመታት ያህል ኾኖት ነበር።" በሚለው ሓረጋዊ አንቀጽ ውስጥ፡ "**ወየአክል**" ማለትም፡ "**የሚያህል**" ተብሎ የተጠቀሰውን ቃል ነበር፡ ለዚያ፡ ቀደም ብሎ ለተወሳው፡ ውሳኔያቸው ዋና መግቢያና ተጨማሪ ምክንያት ያደረጉት።

ይኸውም፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በዚያን በጥምቀቱ ጊዜ፡ ዕድሜው፡ ልክ ሠላሳ ዓመት ሳይኾን፡ ለዚያ መጠን የተቃረበ፥ ወይም፡ ከዚያ መጠን፡ ጥቂት ያለፈ ሊኾን እንደሚችል በመገመት፡ "የጥምቀቱን ቀን፡ በአራት ወራት የወደፊት ልዩነት በማከል፡ ከላይ በተገለጡት ምክንያቶች፡ ወደጥር ፮ ቀን፡ ወስደውታል!" ብሎ መደምደሙ አግባብ ይኾናል።

የሚያስገርመው ግን፡ ባዕዳኑ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን መነኮሳትና ጳጳሳት፡ በመስከረም ፩ ቀን የሚውለውንና የሚከበረውን የልደቱን ቀንና በዓል፡ ወደታኅሣሥ ፳፰/፳፱ ለውጠው እንደወሰዱት ኹሉ፤ አኹንም፡ ያንኑ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ውሳኔ የኾነውን፡ ከመስከረም ፩ ቀን፤ ወደጥር ፩ ቀን ተዛውሮ እንዲከበር ያደረጉትን፡ የጥምቀቱን በዓለ-ዕለት፤ እኒሁ፡ ባዕዳኑ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን መነኮሳትና ጳጳሳት፡ ቀደም ብሎ፡ በበዓለ ጥምቀት መልእክት ላይ፡ በሚበቃ እንደተብራራው፤ አዎን! በሌሎቹ የኢትዮጵያ በዓሎቻችን ላይ ማድረግ እንዳስለመዱት፡ ወደጥር ፲፩ ቀን የለወጡት መኾኑ ይታወቃል።

፪. በመሠረቱ እና በተለይ፡ ሰውን በሚመለከት፡ "'ጥንታዊ ሰብአዊ ፍጡር (Hominoidea)' ተብለው የሚጠሩ፡ አእባነ አዕፅምት አሉ!" በሚለው ዘይቤአቸው፤ *የእየራሳቸውን ዕውቀት፡* የእግዚአብሔር ከኾነው በላይ ያላቁ፡ "የሥነ-ዕውቀቱ ሊቃውንትና ባለቤቶች፡ እኛ ነን!" ያሉ፡ ሰብኣውያን ፍጡራን፡ የሚታመኑበትን፡ የለውጥ ዕድገት ይትበሃላቸውን (Theory of Evolution) ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ አትቀበለውም።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የምትቀበለውና አጽንታ፡ ለዘለዓለም የምታኖረው እምነቷና ምግባርዋ፤ ሥርዓቷና ህልውናዋ ይህ ነው፤ እርሱም፡ እንዲህ በሚል ቃል ይጠቃለላል፦

"እግዚአብሔር አብ እና እግዝእተብሔር እም፤ ከፍጥረት አስቀድሞ፡ በወለዱት ልጃቸው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ፈጣሪነት፤ ከእራሳቸው ባሠረጹትም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት፡ በመልካችንና በአርአያችን፥ "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኹናችሁ!" ብለው፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች፡ ፈጥረው ካኖርዋቸው፥ ኋላም፡ በፍጥረት ፍጻሜ፡ ድንግል ማርያምን እና ኢየሱስ መሲሕን፡ በሰውነት ተዋሕደው፡ በእውነታቸውና በደግነታቸው፥ በፍቅራቸውና በሕይወታቸው፡ ከሓሰትና ከክፋት፤ ከጥላቻና ከሞት ከታደጓቸው [ካዳኗቸው] ከመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፤ በምድር ላይ፡ በሕይወተ-ሥጋ እስከምንኖረው፥ ወደፊትም፡ በዚሁ አኗኗራችን እስከምንቀጥለው፡ እስከወንዱ አዳም እና ሴቷ ሔዋን ድረስ ያለው፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የተዋሕዶ ህልውና የሚኖረው፡ ያው አንዱ ሰው እና ያችው፡ አንዲቷ ሴት ናት።

"መንበረ እግዚአብሔር ጸባዖት" የኾነውን መለኮታዊ ዙፋን የሚሸከሙት፡ አራቱ ሕያዋን ፍጡራን፤ ከዚህ በታች የተጠቀሱት መኾናቸው ይታወቃል፤ እነርሱም፦

**በማቴዎስ የተመሰለው፡** በእግዚአብሔር መልክ ከተፈጠረው ወገን መካከል፡ የኀብስተ-አኰቴትና የጽዋዓ በረከት ተመጋቢ የኾነው፡ ሰው፤

**በማርቆስ የተመሰለው፡** ከአራዊቱ ወገን መካከል፡ ሥጋ-በል የኾነው፡ አንበሳ፤

በሉቃስ የተመሰለው፡ ከእንስሳቱ ወገን መካከል፡ ሣር-በል የኾነው፡ ላሙ፣ እና

በዮሓንስ የተመሰለው፡ ከአዕዋፋቱ ወገን መካከል፡ ኹሉን-በል የኾነው ንስር ናቸው።

እነዚህን የመሰሉት፡ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ አንሥቶ ያሉት ኹሉ፡ ምንም ዓይነት የዕድገት ለውጥ ሳያሳዩ፡ ያው እስከዛሬ፡ በዚያው ባሉበት መልካቸውና ህልውናቸው እየኖሩ እንዳሉ፣ ወደፊትም፡ በዚሁ ይዞታቸው ጸንተው እንደሚቀጥሉ፡ እነሆ፡ በሚታየውና እየደረሰ ባለው እውን ኹኔታ ይታመናል።

ከዚህ የተነሣ፡ ከላይ በተጠቀሱት፡ በዓለማውያኑና በሰብአውያኑ ሊቃውንት ዘንድ፡ "'ጥንታዊ ሰብአዊ ፍጡር (Hominoidea)' ተብለው የሚጠሩት፡ እነዚህ፡ አእባነ አዕፅምት፡ አንዳንድ ወገኖች፡ "በጥፋት ውሃ የነፈሩ አጥንቶች ናቸው" ቢሏቸው አያስደንቅም። የሚያስኬድ ሊኾን ይችላልና።

፫. በኪዳናዊት መስከረም ለቺሳ፡ በኢትየጵያኛ ተተርጉሞ፡ ለገበያ በቀረበው፣ ስለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ትክክለኛ የተዋሕዶ አኗኗር በሚተርከው፡ የቶማስ ሞር መጽሐፍ ውስጥ ስላለው፡ ቀንዳም (ባለ ቀንድ) አንበሳ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ የሚታወቅ ነገር ቢኖር፡ ይኸው ምስል፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ ስድስተኛው የቅዱሱ ኪዳን ምልክታችን ከኾነውና "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ-ይሁዳ" ከሚለው፣ ለኢየሱስ መሲሕ፡ ከተሰጠው፡ ከዘለዓለማዊው የዘውድ ንጉሥነቱ ማኅተም ጋር፡ ፈጽሞ፡ ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው መኾኑ ብቻ ነው።

"ግንኙነት አለው!" ከተባለም፣ ያ ግንኙነት፡ የኢትዮጵያ ልጆች እምነት ከኾነው አንጻር ያለው፡ "ተፃራሪውና ዲያብሎሳዊው ነው!" ማለት ይኾናል።

፬. በኢትዮጵያው ደብረ-ሊባኖስ ገዳም፡ በቀድሞው ዘመን፡ "ተክለ-ሃይማኖት" በሚል ስም የሚታወቁት፡ የቤተ-ክህነት ሰዎች፡ ኹለት ናቸው። የመጀመሪያው፡ በ፯መቶኛው ዓመተ-ምሕረት የነበሩት እውነተኛው ጻድቅና ሓዋርያ ሲኾኑ፣ ኹለተኛው ደግሞ፡ በ፲፫መቶኛው ዓመተ-ምሕረት የኖሩት፣ በአንተም የእ-ጦማር ጽሑፍ፡- «"ዛጌዎች" ተብለው የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አጼዎችን፡ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" ከሚሉ መነኮሳት ጋር በመተባበር፡ መለኮታዊውን የዘውድ ዙፋን፡ በዋነኛ የእጨጌነት ግንባር ቀደም ተዋናይነታቸው፡ ወደሰውኛው ለውጠው፡ "የሰሎሞን ዘር ነን!" የሚሉትን ወገኖች፡ ለአጼነቱ የሹመት ሓረግ ያበቁት ናቸው!» ያልሃቸው ናቸው።

የእኼህኛውን የኹለተኛውን፡ የእጨጌ ተክለ ሃይማኖትን፡ ይህን ምግባር፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ምንጊዜም አጽድቃ አልተቀበለችውም።

\+ \+ \+